# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጳጉሜ 2 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**በእርስ በርስ ንትርክና ጭቀጭቅ የተወጠረ የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ድንገተኛ ስብሰባ ተደረገ፤**

**በያወኔ የጦር አለቆች ውስጥ ችግር መኖሩ ተወራ፤**

**ሌላ ዙር የግዳጅ መዋጮ ዘመቻ ተጀመረ፤**

የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከማክሰኞ ነሐሴ 29 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ተከታታይ ቀናት አስቸኩዋይ ስብሰባ ማድረጉ ታወቀ::

መለስ ከሞተ በኋላ ለመጀመሪያ ግዜ በተደረገው የስራ አስፈጻሚው አስቸኩዋይ ስብሰባ ላይ የወያኔ ባለስልጣኖቸ በብዙ አጀንዳዎች ዙሪያ ሳይስማሙ እንደሰነበቱም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

ከ36 ስራ አስፈጻሚዎች መሀከል 33 አባላት የተገኙበት ስብሰባ ዋነኛና አወዛጋቢ አጀንዳ የነበረው የኃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆንና አለመሆን እንደነበር ምንጮቹ ገልፀዋል::

የወያኔ ስራ አስፈፃሚ 36 አባላት የነበሩት ሲሆን ከነዚህ መሀከል ከህወሀት መለስ ዜናዊ በሞት ..... ሌላ ሁለት አባሎች ደግሞ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ሳይገኙ ቀርተዋል::

መለስ ሞተ ተብሎ በተነገረ ጥቂት ሰዓት ውስጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኃይለማርያም ደሳለኝን ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ስልጣን ሰጥቶት እንዲሰራ ውሳኔ ያሳለፈ ቢሆንም ጥቂት የህወሀት ሰዎች ባነሱት ተቃውሞ መልሰው የሰጡትን ስልጣን ቀምተው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በመባሉ ዙሪያ በስራ አስፈፃሚው ስብሰባ ላይ ተነስቶ የከረረ ውዝግብ መደረጉን የቤተ መንግስት ምንጮች ገልጸዋል::

ብአዴኖች ከህወሀት ጋር የቃላት ፍልሚያ ሲያደርጉ ኦህዴዶችም ሚናውን ባልለየለት ሁኔታ በፊናቸው የውዝግቡ አንዱ አካል ሆነው የሰነበቱ መሆኑን ያጋለጠው የምንጮቹ ጥቆማ በተለይ በበረከት

የሚመራው የብአዴን ቡድን ጠንክሮ በሀሳብ የበላይነቱን ይዞ እንደሰነበተም ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በሀዘኑ ግዜ አንድነቱን ላሳየን ህዝብ አክብሮት ሰጥተን በቀጣይ ወደ ስራ ለመግባት እንዲያመቸን የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ስልጣን በይፋ መግለጽ አለብን በማለት ብአዴኖች በግልጽ ሀሳብ ያቀረቡ ቢሆንም የህወሀት ሰዎች ግን የተወካዮች ምክር ቤት ስራ እስኪጀምር መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ ድረስ አሁን ባለው ሁኔታ በድፍኑ ይቀጥል በማለት በተነሳ አተካሮ አንድ ቀን ሙሉ ሲነታረኩ ከመዋላቸውም በተጨማሪ ባለመግባባታቸው የተነሳ ማክሰኞ ዕለት እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት ድረስ እንዳመሹም ታውቋል፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት አምኖበት ኃይለማርያምን ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር ብሎ ሰይሞ ሹመቱም በሚዲያ ተገልጾ ለአንድ ቀን ከቆየ በሁዋላ ማን ስልጣን ሰጥቶዋችሁ ነው ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር ብላችሁ የምትጠሩት በሚል ህወሀቶች በማግስቱ እንዲቀየር እና ወደ ነበረበት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ እንዲመለስ ማስገደዳቸውም የህወሀት የበላይነት ዘመቻ አንዱ አካል እንደሆነ ተጠቁሞዋል፡፡

የደኢህዴን ሊቀመንበር እና የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር ኃይለማርያም ደሳለኝ በበኩሉ በመበሳጨት አስፈላጊ ከሆነ እንኩዋን የመለስን ቦታ ይቅርና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ስልጣን መውሰድ የምትችሉ ሲሆን ከእንግዲህ እኔን በተመለከተ አንዳችም ውዝግብ በመሀከላችሁ ሊፈጠር አይገባም በማለት ውጥረቱን ለማርገብ ሲሞክርም እንደተደመጠ ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ስልጣን ከእጃቸው ቢወጣ ሰማይ የተደፋባቸው የሚመስላቸው ህወሀቶች በዚሁ ለሁለት ቀናት በተደረገው አስቸኩዋይ ስብሰባ ባቀረቡት ሀሳብ ላይ አንዳሉት ከሆነ የኢህአዴግን(ወያኔ) ሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር የመሰየም ጉዳይ የግንባሩ ምክር ቤት ስልጣን ነው በሚል ሰበብ በስብሀት ነጋ አቀነባባሪነት በእነ ፀጋዬ በርሄ አቅራቢነት ሹመቱ እንዳይከናወን ሰፊ ዘመቻ መድረጋቸው ታውቆዋል፡፡

በዚህም መሰረት በመጪው መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ በኢህአዴግ(ወያኔ) ምክር ቤት የሚመረጡት ሊቀመንበሩና ምክትል ሊቀመንበር የሀገሪቱን አመራር ሙሉ ለሙሉ ይረከባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም የቤተመንግስት ምንጮች ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በሞት መለየቱን በይፋ አውጀው ከገለጹ በሁዋላ በምትኩ ምክትሉ ስልጣኑን መረከብ ሲገባው ከበረሀ ያልመጣ ሰው ስልጣን አይዝም..... ማን በሞተበት ማን ይሾማል ......ቦታው ዛላለማዊ በሆነ መልኩ የህወሀት ብቻ ነው .....የሚሉ ምክንያቶችን በመደርደር እነ ስብሀት ነጋ በስውር በሚመሩት ቡድን አማካኝነት ዘመቻ እያከሄዱ መሆናቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ዴሞክራሲ ያልሰፈነበት ሀገር ውስጥ ስልጣን በተዋረድ ለማስረከብ ጣር እንደሆነና ወያኔም የዚሁ ዋነኛ ተዋናይ በመሆኑ ግራ ገብቶት እርስ በርስ ሲታመስ እየተስተዋለ ከመሆኑም በላይ ህዝቡ ደግሞ ከመቼውም ግዜ በላይ በቡድኑ ላይ እምነት እንደሌለው ያረጋገጠበት ወቅት ነው ሲሉ አንዳንድ ምሁራን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ሰሞኑን ትሸማለህ አትሸምም እየተባለ በሁለት ቡድን መሀከል አጣብቂኝ ውስጥ የገባው ሃይለ ማርያም ደሳለኝ በወላይታ ዞን ሐምሌ 12 ቀን 1957 ዓ.ም ተወልዶ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም በዚያው ያጠናቀቀ መሆኑን የጠቆሙት አብሮ አደጎቹ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የእና በፊንላንድ ቲምበር ዩኒቨርስቲ በውሀ ምህንድስና ሙያ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ያገኘና በአርባ ምንጭ የውሀ ቲክኖሎጂ ኢንስቲትት ከመምህርነት እስከ ዲንነት ለ13 ዓመታት ሲያገለግል የቆየ መሆኑን አትተው በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ የወያኔ አባል ከሆነበት ግዜ ጀምሮ ከሌሎቹ በበለጠ ሁኔታ ፈጣን እና ንቁ ተሳታፊ በመሆኑ መለስ ዜናዊ ለክልሉ ፕሬዝዳንትነት ሊመረጠው እንደቻለ ገልፀዋል፡፡

ቀድሞ የነበረው የደኢህዴን ሊቀመንበር እና የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት አባተ ኪሾም በተመሳሳይ ከመምህርነት ተነስቶ የመጣ መሆኑን ያስታወሱት የደቡብ ተወላጆች በህወሀት ውስጥ በ1994 ዓ.ም በተፈጠረ ክፍፍል ምክንያት አባተ ኪሾ የአንጃው ቡድን ደጋፊ ነህ ተብሎ ለእስር በተዳረገበት ወቅት ድንገት ተመርጦ የመጣው ኃይማርያም ደሳለኝ መሆኑን ገልፀው በተሾመ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በሲዳማ ህዝብ ላይ በአዋሳ ከተማ አቅራቢያ ሎቄ ከተማ ውስጥ እጅግ ዘግናኝ ጭፍጨፋ እንዲፈጸም ከመለስ ጋር በመሆን መመሪያና ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑንም ጨምረው ይገልጻሉ፡፡

በተያያዘ ዜና በህወሀት ቡድን እምቢ ባይነት ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን የተነጠቀው ኃይለማርያም ደሳለኝ ለመጀመሪያ ግዜ ሰኞ ነሐሴ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ምሽት ላይ በቲሌቪዥን ለህዝብ በይፋ ንግግር አደረገ፡፡

እጁ እየተንቀጠቀጠ .....አይኑ እየተርገበገበ..... ፊደሎቹን እየዘለለ......በዚሁ ባደረገው ንግግር እስከ ዛሬ ተሰምቶና ታይቶ ባልታወቀ ሁኔታ ማጀት ውስጥ በስራ ላይ ያሉትን ጥቂት ዜጎች ጭምር እያነሳ የተከበራችሁ በሚል መደለያ ቃል ሲማጸን እንደነበር የተደመጠ ሲሆን ነባርና አዳዲስ አመራሮች በጋራ በመሆን መለስ የጀመራቸውን ውጥኖች እንጨርሳለን ሲልም በመናገሩ ለውጥ አለመኖሩን አሳይቶዋል፡፡

ቦዘኔ...ወሮበላ.....ነጣቂ...ዘራፊ... እያሉ ሲያወግዙዋቸውና ሲያብጠለጥሉዋቸው አልፎ ተርፎ እንደ ሰው ሳይቆጥሩዋቸው የነበሩትን ወያኔ በፈጠረው ችግር ምክንያት የጎዳና ተዳዳሪ የሆኑትን ዜጎች ጭምር በቃላት ሊያታልል እና አንጀት ሊበላ የተከበራችሁ እያለ ሲማጸን እንደነበርም ተደምጦዋል፡፡

እግረ መንገዱን በወያኔ ቡድን ውስጥ ችግር መኖሩን የጠቆመው በለስ የቀናው..... ከአርባ ምንጭ የመጣው ......የወላይታ ተወላጁ ኃይለማርያም ደሳለኝ በተለይ በአሁንዋ ሰዓት ፈታኝ የሆኑ ጉዳዮች ከፊታችን ተጋርጠዋል ሲልም በቡድኑ ውስጥ ያለውን ችግር በይፋ አጋልጦዋል፡፡

በግዳጅ እና በውሎ አበል ክፍያ አደባባይ የወጣውን ህዝብ «ለመለስ ለቅሶ ያሳየውን ተሳትፎ ለማመስገን» በሚል ባቀረበው በዚሁ አጭር የምስጋና ንግግር ህዝቡ ከጎናቸው እንዲቆም የተማጸነ ከመሆኑም በላይ የተጀመረውን የአባይ ግድብ ለመጨረስ መዋጮ ግድ እንደሚልም ተናግሮዋል፡፡

ቤተ መንግስት በለቅሶው ሰበብ ለመጎብኘት የገባው ወጣት በምሬት እና በብስጭት መለስንና በረከትን ሲያወግዙ እንደነበርም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋለጠ::

ረቡዕ ነሐሴ 23 ቀን 2004 ዓ.ም በቤተ መንግስት ውስጥ «**መለስ ዕዳ አለብህ፤በረከት የሀገር እና የህዝብ ጠላት ነው ስልጣን እንዳይሰጠው**» የሚሉ ጩኸቶች ተስተጋብቶ እንደነበርና ይሄንኑ ለማርገብ ተብሎ ቀይ ቆብ ያጠለቁት የቤተ መንግስት ጥበቃ ወታደሮች ወጣቶቹን በማግባባት በሌላ በር ከግቢ እንዲወጡ እንዳደረጉዋቸው ይሄው የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አጋልጠዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኦህዴድ .....የህወሀት እና የኢህአዴግ ሊቀመንበሮችን ለመምረጥ ውስጥ ውስጡን ሰፊ ዘመቻ መጀመሩን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የደረሱን ጥቆማዎች ገለጹ::

ሰሞኑን በደረሰን ጥቆማ መሰረት ህወሀቶች የድርጅቱን ህልውና በበላይነት ሊያስቀጥል የሚችል እና ኢህአዴግን ጭምር ሊመራ የሚችል ጠንካራ ሰው መመረጥ አለበት በሚል እርስ በርሳቸውም ጠንካራ ፉክክር መያዛቸው ታውቆዋል::

በስብሀት ነጋ የሚመራ አንድ ስውር ቡድን በህወሀትም ሆነ በኢህአዴግ ውስጥ ተሰሚነት ያለው የህወሀት በረሀ አመጣሽ ሰው መሾም አለበት በሚል አባይ ጸሐዬ እንዲሾም ከፍተኛ ቅሰቀሳ እያደረገ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ከዚህ በፊት መለስን ክዶ በአቁዋሙ ሳይጸና የተመለሰ በመሆኑ አሁንስ እኛን የማይክድበት ምክንያት አለ? በሚል እርስ በርስ እየተወዛገቡ እንደሚገኝም ተጠቁሞዋል::

በመስከረም ወር መጀመሪያ ላይ የኢህአዴግ ምክር ቤት አስቸኩዋይ ስብሰባ የሚያደርግ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ከዚያ በፊት ህወሀቶች ሊቀመንበራቸውን መርጠው መሾም እንደሚገባቸው ስለሚያውቁ ከወዲሁ እየተሩዋሩዋጡ እንደሚገኙና ከስብሀት ነጋ በተቃራኒ የቆመው ቡድን ደግሞ በአሁኑ ሰዓት የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት የሆነውን አባይ ወልዱ የተባለውን ግለሰብ የህወሀት ሊቀመንበር አድርጎ ለመሾም እየሰራ መሆኑም ተጠቁሞዋል::

የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቲም በበኩሉ ስራ ሳይሰራ ለበሽታ በተዳረገውና የመለስ ቀኝ በነበረው የኦህዴድ ሊቀመንበር እና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አለማየሁ አቶምሳ ምትክ አቁዋመ ጠንካራ.....ለየትኛውም የማያጎበድድ.....በራሱ የሚተማመን.....የተማረና ወጣት መሆን አለበት በሚል የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች የየራሳቸውን ቅርብ ሰው እያዘጋጁ መሆኑም ታውቆዋል::

በኦህዴድ ባለስልጣናት በኩል የተጀመረው ዘመቻ ደግሞ በየጎጣቸው እና በየመንደራቸው ተከፋፈለው የባሌ... የአርሲ... የሐረር...... የሸዋ...... የወለጋ...... የጅማ..... የቦረና... ተወላጅ መሆን አለበት በሚል እርስ በርስ ሲነታረኩ የሚገኝ ቢሆንም አሁንም ክልሉን በበላይነት በስውር እየመራ የሚገኘው የህወሀቱ ገብረተንሳይ ወ/ተንሳይ የተባለው ግለሰብ በመሆኑ ኦህዴድ አዲስ አመራር ሾመም አልሾመ ብዙ ለውጥ አያመጣም እየተባለ ይገኛል::

ልክ እንደ ካድሬዎቹ ሁሉ ወያኔ ጄኔራል እያለ በሚጠራቸው የጦር አለቆች መከከልም መሀከል የሃሳብ ልዩነት ተፈጥሮ እርስ በርስ ተከ዗ዋርፈው የሚገኙ መሆኑን የጠቆሙት የመከላከያ የውስጥ አዋቂ

ምንጮች በጡረታ የተሰናበቱ የጦር አለቆች ወደ ስራ እንዲመለሱ ጥያቄ እያቀረቡላቸው እንደሆነም ምንጮቹ ገልፀዋል::

በጡረታ የተሰናበተውን የኦህዴዱን ባጫ ደበሌን ወደ ስራው እንዲመለስ በከፍተኛ የኦህዴድ ባለስልጣናት እና በሚቀርቡት የጦር አለቆች በኩል የተጠየቀ ቢሆነም መኪና ንግድ ላይ የተሰማራው ባጫ እስከ ቅርብ ቀን ድረስ መልሱን ያልሰጠ መሆኑንም ምንጮቹ ገልጸዋል::

በአሁኑ ሰዓት በመከላከያ የጦር አለቆች መሀከል የእርስ በርስ መናናቅ የተፈጠረ ሲሆን በወያኔ ኤታማጆር ሹሙ ሳሞራ የኑስን አንዳንድ የህወሀት የጦር አለቆች በራሱ የማይተማመን በማለት እያናናቁት መሆናቸው ይነገራል::

የማዕከላዊ እዝ ዋና አዛዥ የሆነው የብአዴኑ አበባው ታደሰ በወያኔ ከተመደቡት ወታደራዊ ማዕረጎች ውስጥ ሶስተኛ ደረጃ ላይ ያለ ቢሆንም እስከ አሁን የአንድ እዥ አዛዥ አድርገው ሽሬ ከተማ እንዲቀመጥ ከመደረጉም በላይ በ1997 ዓ.ም ከተደረገው ምርጫ ጋር ተያይዞ ከተቃዋሚ መሪዎች ጋር ግንኙነት አለህ በሚል ብዙ ጫናዎች ሲደረጉበት እንደነበር እና አሁን ግን ደፍሮ መናገር መጀመሩንና የራሱን ተከታይ እያፈራ መምጣቱን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል::

በመጨረሻም በመለስ ሞት ምክንያት ለ13 ቀናት በመላ ሀገሪቱ ለካድሬዎች አበል፤ለትራንስፖርት፤ለፖስተር እና ለሌሎችም በሚል ከህዝብ ካዝና በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ሲረጩ የከረሙት የወያኔ ባለስልጣናት ሰሞኑን ህዝቡ በግዳጅ ለቦንድ እንዲያዋጣ ብለው የስንግ እየያዙት መሆኑ ታወቀ::

በዚሁ ባሳለፍነው 15 ቀናት ውስጥ በሀገሪቱ ከፍተኛ የዋጋ ንረት ተፈጥሮ ህዝቡ ግራ ተጋብቶ የሚገኝ ሲሆን ጤፍ አንድ ኩንታል ከ1500 ብር ወደ 2 ሺህ200 ብር ማሻቀቡንና ቀይ ሽንኩርት ከ6 ብር ወደ 20 ብር መሽቀንጠሩን ተከትሎ የጥራጥሬና ሌሎች ቁሳቁሶችም ዋጋ መናሩ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ የኑሮ ጫና ፈጥሮ እያለ የወያኔ ቡድን እንደገና መዋጮ በሚል አዲስ ዘመቻ መጀመሩ ታውቋል::

ህዝቡ ኑሮ ከብዶት አምላኩን እየለመነ ባለበት በዚህ ግዜ ማሰቢያ የሌላቸው የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት መለስ የጀመረውን የህዳሴ ግድብ እናስጨርሳለን በማለት የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ፍጹም ያላገናዘበ መዋጮ እንዲያከናውን ማዘዛቸው ለሕዝብ ደንታ የሌላቸው መሆኑን ያሳያል:: የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች የነሐሴ ወር ደመወዝ እስከ ዛሬ እንደልተከፈላቸውም ጨምረው ገልፀዋል::

የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት በመሀከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት ለመሸፈንና ግዜያዊ ፋታ ለማግኘት ሲሉ የህዝብን ሀብት በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ከመንግስት ካዝና እያወጡ ሲበትኑ ከርመው አሁን ደግሞ የመለስን ራዕይ እናሳካለን በሚል ህዝቡ በግዳጅ በአዲስ መልክ ለአባይ እንዲያዋጣ እያስገደዱት መሆኑም ታውቋል::

ሰሞኑን በተጀመረው ዘመቻ መሰረት የመንግስት ሰራተኛውም ሆነ የግል ድርጅት ሰራተኛው ኑሮን መቋቋቋም  አቅቶት እየተንገዳገደ ባለበት በዚህ ግዜ ለሁለተኛ ዙር የአንድ ወር ደመወዛቸውን በዓመት እንዲከፍሉ የሚያስገድድ መመሪያ መተላለፉም ታውቆዋል፡፡

ከዚህም ሌላ የደመወዝ ጭማሪ እና እድገት የተነፈገው ሰራተኛ መለስ የወጠናቸውን ጅምሮች ለማጠናቀቅ በሚል የዕረፍት ቀኑን በመንጠቅ ቅዳሜ የስራ ቀን እንዲሆን ሊወሰን በየመስሪያ ቤቱ ዘመቻ መጀመሩን ተከትሎ ተቃውሞ እያጋጠመው መሆኑንም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ያለውን የኑሮ ጫና ለመቋቋቋም ባለችው ትርፍ ሰዓት ተሩዋሩጦ እንዳይሰራና ቤተሰቡን እንዳይደጉም ቅዳሜን የስራ ቀን እንዲሆን ለመወሰን እየተራወጡ በመገኘታቸው በተለያዩ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች እየተቃወሙ መሆኑም ታውቆዋል፡፡